# ብሔርተኝነት ያደርሳል ከጦርነት፣ ያመጣል ጨቋኝ ስርዓት (ክፍል-1)



**June 24, 2017**

ስዩም ተሾመ

ከዚህ ቀደም "የአማራ-ብሔርተኝነት ከየት ወደየት?" የሚል ፅኁፍ ፅፌ ከጨረስኩ በኋላ በስህተት ከኮምፒውተሬ ውስጥ ስላጠፋሁት ሳይታተም ቀረ። ፅኁፉ በዋናነት "ቤተ-አማራ" የሚባለው ቡድን በሚያቀነቅነው የአማራ-ብሔርተኝነት ላይ ያጠነጠነ ነበር። በእርግጥ እንደ ኢህአዴግ ያለ ጨቋኝ ስርዓት ዜጎች የሚያነሱትን የእኩልነት፣ ነፃነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄን በኃይል ማፈን ባህሪው ነው። የመብትና ነፃነት ጥያቄ በኃይል ሲታፈን ደግሞ የማህብረሰቡ የፖለቲካ ልሂቃን የብሔርተኝነት ስሜት ማቀንቀን ይጀምራሉ።

"የአማራ ብሔርተኝነት" መነሻ ምክንያት የአማራ ሕዝብ የመብትና ነፃነት ጥያቄ በኃይል መታፈኑ ነው። በመሰረቱ "ብሔርተኝነት" የሕዝብ ንቅናቄ ለመቀስቀስ (mobilization) እና ለማዳፈን (demobilization) ዋና መሳሪያ ነው። የመከፋፈል መርሆችን (Principles of division) በማስቀመጥ የሚታወቀው ፈረንሳዊው ተመራማሪ "Bourdieu" የአንድ ሀገር ሕዝብን የመከፋፈል መሰረታዊ ዓላማና ግብን እንዲህ ይገልፀዋል፡-

> *"Principles of division function within and for the purposes of the struggle between social groups…What is at stake in the struggle is power over the classificatory schemes and systems which are the basis of the representations of the groups and therefore of their mobilization and demobilization: the evocative power of an utterance which puts things in a different light" Distinction. A social critique of the judgement of taste, 1984.*

ከዚህ አንፃር፣ ለምሳሌ የቀድሞ የሕውሃት መስራችና አመራር አረጋዊ በርሄ የትግራይ ሕዝብ የመብትና ነፃነት ጥያቄ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ እና በደርግ መንግስት በኃይል ሲዳፈን የትግራይ ልሂቃን የብሔርተኝነት ስሜትን ማቀንቀን እንደጀመሩ ይገልፃል። በመጨረሻም፣ በብሔርተኝነት ስሜት በመቀስቀስ (mobilization) እና በራስ-የመወሰን መብትን (rights of self-determination) ተስፋ በመስጠት የሕወሃት የትጥቅ ትግል ተጀመረ። በሕወሃት መሪነት የተመሰረተው ኢህአዴግ የደርግ ስርዓት ከስልጣን ካስወገደ በኋላ በብሔር-ልዩነት ላይ የተመሰረተ የአፓርታይድ ስርዓት ዘረጋ።

የብሔር-አፓርታይድ ስርዓት ዓላማና ግብ ደግሞ በሀገሪቱ አብላጫ ድምፅ (majority) ያላቸውን የኦሮሞና አማራ ሕዝብ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዳፈን (demobilization) ነው። ለዚህ ደግሞ ባለፉት አስር አመታት የኢህአዴግ መንግስት የግምገማ ሪፖርቶች ውስጥ "ትምህክተኝነት" እና "ጠባብነት" የመንግስታዊ ስርዓቱ አደጋዎች በሚል ያልተገለፁበት ግዜ የለም። ብሔርተኝነትን እያቀነቀነ ወደ ስልጣን የመጣው ሕወሃት መራሹ የፖለቲካ ቡድን የአማራና ኦሮሞ ሕዝብን የመብትና ነፃነት ጥያቄ "ትምክህተኛ" እና "ጠባብ-ብሔርተኛ" እያለ ያሸማቅቃል። "ትምክህተኛ" እና "ጠባብ-ብሔርተኛ" የሚሉት "Bourdieu" – "*the evocative power of an utterance which puts things in a different light''* የሚለው ዓይነት ፋይዳ ያላቸው ቃላት ናቸው።

በአጠቃላይ፣ ብሔርተኝነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ንቅናቄ የሚወስደው ወደ እርስ-በእርስ ጦርነት ሲሆን መጨረሻው ደግሞ ጨቋኝ ስርዓት መፍጠር ነው። በምንም ዓይነት ተዓምር ቢሆን የብሔርተኝነት ንቅናቄ ወደ ዴሞክራሲ አያደርስም። በመሆኑም፣ ብሔርተኝነት ለሚታገሉለት ሕዝብ መብትና ነፃነት ሆነ ለጎረቤት ሀገር ሰላምና ደህንነት አይበጅም። ለምሳሌ፣ ብሔርተኝነትና በራስ-የመወሰን መብትን ዓላማ አድርገው የተነሱት ሕወሃትና ሻዕቢያን እንመልከት።

በራስ-የመወሰን መብት በክልል ደረጃ ራስን-በራስ ከማስተዳደር እስከ መገንጠል ሊደርስ ይችላል። ሕወሃት ብሔርተኝነት እያቀነቀነ በጀመረው የትጥቅ ትግል አሸንፎ የትግራይ ሕዝብን ራስን-በራሱ እንዲያተዳድር አደረገ። ነገር ግን፣ መብትና ነፃነትን ከማረጋገጥ አንፃር ግን የኢህአዴግ የብሔር ፖለቲካ ለትግራይ ሕዝብ ሆነ ለተቀረው የኢትዮጲያ ህዝብ ከአምባገነንነት ሌላ ያመጣው ትርፍ የለም። በተመሳሳይ፣ የኤርትራ ብሔርተኝነት እያቀነቀነ የትጥቅ የጀመሩት የኤርትራ አማፂያን ከኢትዮጲያ በመገንጠል የራሳቸው ሉዓላዊ ሀገር መሰረቱ። ነገር ግን፣ አሁንም ድረስ የታሪክ ቁስል ከማከክ በዘለለ የኤርትራዊያንን መብትና ነፃነት አልተከበረም። የትጥቅ ትግል ከጀመሩበት የቀዳማዊ ኃ/ስላሴ መንግስት ቀርቶ ከወታደራዊ ደርግ የባሰ ጨቋኝና ጦረኛ የሆነውን የሻዕቢያ መንግስት ከመፍጠር ባለፈ በኤርትራዊያን መብትና ነፃነት ሆነ በጎረቤት ሀገሮች ሰላምና ደህንነት ላይ ያመጡት ለውጥ የለም።

በአጠቃላየ፣ በብሔርተኝነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መቼም ቢሆን የብዙሃንን መብት፣ ነፃነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አያስችልም። የብሔርተኝነት መጨረሻ ጦርነትና ጨቋኝ ስርዓት ነው። ምክንያቱም፣ የብሔርተኝነት ፅንሰ-ሃሳብ በራሱ ከነፃነት ይልቅ በጠላትነት እሳቤ ላይ የተመሰረተ ነው። ብሔርተኝነት የሰው-ልጅን ሰብዓዊነት ገፍፎ ከተራ እንስሳት በታች ያደርገዋል። በእርግጥ አገላለፁ ኃይለ-ቃል የተቀላቀለበት ወይም ግነት የበዛበት ሊመስል ይችላል። ነገር ግን፣ እውነታው ይሄ ነው። ብሔርተኝነት ሰውን ከተራ እንስሳት ለምሳሌ፣ ከቀበሮ፥ ጅብ፥ ውሻ፥… በታች ያደርገዋል። በኢ-ሰብዓዊነት እሳቤ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ንቅናቄ መጨረሻው የሰዎችን ሰብዓዊ መብትና ፖለቲካዊ ነፃነት የሚገፍፍ ጨቋኝና ጦረኛ መንግስታዊ ስርዓት መመስረት ይሆናል። በቀጣዩ ክፍል "ለምንና እንዴት?" የሚለውን በዝርዝር እንመለከታለን።